

ፍጹም መንገሻ (ከኖርዌይ)

# ሃገር አድኑን ትግል እናግዝ እንቀላቀል

ሃገራችን ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሃገራት ከቅኝ አገዛዝ ነጻ መውጣት ለጥቁር ህዝብ ነጻነት ያበረከተችው አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል እንዳልሆነ የሚታወቅ ነው።ከዚህም በተጨማሪ ለሙስሊሙ እምነት ባለውለታነቷን ታሪክ የሚፍቀው አይሆንም።ይህ መልካም ተግባሯ በሌላ በኩል ሃገራችንን በአይነቁራኛ እንዲመለከቷት እና አሁን በአይናችን እንደምናየው ባንዳዎችን ቀጥረው እስኪበቀሏት ዳርጓታል።የዛሬው ታሪክን ማጥፋት ሩጫም የነዚሁ ውጤት ሳይሆን አልቀረም። አሁን በሃይል ቦታውን የተቆጣጠረው አገዛዝም ህዝብን በማሰቃየት እና ወደተለያየ ሃገራት በማሰደድ እየተራዳ ለዚሁ የብቀላ ድርጊት ተዋናይነቱን እያሳየ ይገኛል።በየሃገራቱም ያሉ መንግስታት ይህ ህዝብ ተወካይ እና ተጠሪ ያጣ እንደሆነ በመረዳት እስኪመስል እንደፈለጉ እያሰቃዩት ይገኛሉ።

ዛሬ በተለይም አፓርታይድን በመዋጋት ነጻ የወጣችው በሚባልላት ለነጻነቷም ባደረገችው ትግል ከጎኗ የቆምንላት ለነጻነቱዋ ዋና ናቸው የተባሉትን መሪዋን ከራሳችን የነጻነት ተዋጊዎች አብልጠን የምናወድስላት እና የሸለምንላት በደቡብ አፍሪካ፡- እንደዚሁም እራሳቸውን ለሚሰዉለት የእስልምና እምነታቸው መቀጠል ከፍተኛ እና የማይረሳ ውለታ በዋልንላቸው በየመን በሱዳን በአረብ ሃገራት በርካታ ወገኖቻችን መከራና ስቃይ እያሳለፉ ይገኛሉ። ይህንንም የኢትዮጵያ ህዝብ አንጀቱ እያረረ በተለያዩ ሚዲያዎች እየተከታተለው ይገኛል። በሃገር ውስጥ ያለው ህዝብ ለዚህ ሁሉ ስቃይ ተጠያቂ በሆነው አካል ወይም አገዛዝ ድርጊቱን ለማውገዝ እና የወገኑን ድምጽ ለማሰማት ቢከለከልም በውጭ የሚገኘው ህዝባችን በበርካታ ሃገራት ድርጊቱን ለማውገዝ ሰልፎች እና ተቃውሞዎች እየተጠሩ እና እየተደረጉ ናቸው። ከዚህ በፊትም እንደዚህ ዓይነት አሰቃቂ ድርጊቶች በወገኖቻችን ላይ ሲደርስ ተመሳሳይ ተቃውሞዎች በድርጊቱ ፈጻሚ ሃገራት ኤምባሲ እና በሚመለከታቸው ድርጅት ጽህፈት ቤቶች ፊትለፊት ተደርገዋል። የህዝብን ድምጽ ማሰማቱ የሚደገፍም ነው። ነገር ግን

ይህ ድርጊት እንዳይቀጥል ከተፈለገ ከባለፈው ተሞክሮ በየኤምባሲዎች እና በየድርጅቶ መጮሁ የተገኘውን ውጤት መመርመሩ ተገቢ እና ለወደፊቱ አመላካች ሊሆን ይችላል።

በርግጥ በዚህ ወቅት የኢትዮጵያን ህዝብ ስቃይ ጬኸት የሚሰማ አካል አለን?

ያለው አገዛዝስ እውነት ይህ የእያንዳንዳችንን አንገት ያስደፋን እና ያሳቆጬንን ድርጊት

እንደኛ ተቆጭቶና ተቆርቁሮ ያየዋልን? ወይስ አገዛዙ ለቆመለት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት እና ማዋረድ የድል ብስራት ነው? ብሎ ማጠየቁም ተገቢነው ትናንት በሳኡዲ ተመሳሳይ ሰቆቃ ተፈጸመ ተወገዘ ተጮኸ ተረሳ በተለያዩ ሃገራትም ቀጠለ ዛሬ ደግሞ የአለምን ሚዲያ እስከሚቆጣጠር ሁኔታው ተባብሶ ቀጠለ። ዛሬም ከባለፈው ጬኸት እና ማውገዝ አንድ እርምጃ እስካልገፋን ድረስ ሁኔታው ከዚህ በባሰ መጓዙ እና ለአገዛዙም መሳለቂያ መሆን አይቀሬ ነው። አሁን በየሃገራቱ እየተፈጸመብን ያለው ወንጀል የተወሰነውን የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላ የኢትዮጵያን ህዝብ የሚመለከት አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ይህም የሚያሳየን አገዛዙ ለፖለቲካ ጥቅሙ ቢከፋፍለንም ችግር ሲመጣ በጋራ እንደሆነ ሁሉ ጠቃሚ ነገርም ቢመጣ ለሁሉም መሆኑን እናይበታለን በተጨማሪም መቼም ቢሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ተለያይቶ መጠቀምም ሆነ መቸገር አለመቻሉን ነው። ይልቁንም ካለው የዓለማችን ለውጥ አኳያ ወደ ፊትስ ምን ይመጣል? በየሃገራቱ ተሰዶ ያለው ህዝባችን ምን ይጠብቀዋል? እንደኛ አይነት ተቆርቋሪ ወይም የሚወክለው መንግስት የሌለው ህዝብ ምን ሊገጥመው ይችላል? ከሚለው በመነሳት የግድ ሃገራችንን ከሃገር አጥፊው አገዛዝ ማላቀቁ ከዛሬው ብቻ ሳይሆን ከመጭው ችግር እራስንመጠበቅ እንደሆነ እና ብቸኛ መፍትሄ መሆኑን ያሳያል።

ታዲያ መፍትሄው ምን መሆን አለበት?

1ኛ **በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ህዝብ በራሱ የመረጠው እና የሚወክለው አካል ወይም መንግስት እንደሌለው ማወቅ እራሱ የመረጠው መንግስትእስከ ሌለ ድረስም ይህ ሁኔታ እንደሚቀጥል በመረዳት በህዝብ የተቋቋመ ለህዝብ የሚቆረቆር መንግስት ማቋቋም እንዳለበት መገንዘቡ አስፈላጊ ነው።**ይህን ለመወሰን ደግሞ ህዝባችን በአገዛዙ የደረሰበትን ግፍ እና መከራ ግድያ ፤እንደ ሁለተኛ ዜጋ እየታየ ከመሬቱ እየተፈናቀለ ለባእዳን መሰጠቱ ፤አሁን ሰአት በተለያዩ ሃገራት እየተፈጸመ ያለውን ብሄራዊ ውርደት፤ ሆን ተብሎ በኑሮ ውድነት መሰቃየት እና ሌሎቹም እንደዚሁም ሃገራችን ለፖለቲካ ትርፍ ሲባል ብቻ በየጊዜው የምታጣውን ለም መሬት፤ የታሪክ ማጥፋት እሩጫ፤ የእርስ በርስ ማጋደል የመከፋፈለል እሩጫ ሌሎችም ተወርተው የማያልቁ ችግሮችን ማስታወስ በቂ ነው። እዚህ ላይ ስርአቱ

ይህን ድርጊቱን ለመሸፈን የሚጠቀምበትን የልማት የእድገት የአባይ ግድብ የመሳሰሉ የማደናገሪያ እና የተሳሳተ ፕሮፓጋንዳንም መመርመር የግድ ነው።

2ኛ የኢትዮጵያ ህዝብ ከጨቋኙ እና ከሃገር አጥፊው አገዛዝ ለመላቀቅ እራሱ የኢትዮጵያ ህዝብ እንጂ ሌላ እንዳልሆነ በመገንዘብ እርስ በርስ መወያየት እና አንድ መሆን አማራጭ የሌለው ነገር እንደሆነ በማወቅ ለስርአቱ እድሜ ማራዘሚያ የሆነውን ልዩነት ማስወገድ እና እና በጭራሽ ተለያይቶ መኳዝ እንደማይችል በመገንዘብ አንድነቱን በማጠናከር ህዝብ በሙሉ አንድ ሆኖ መነሳት ግዴታው ነው።

3ኛ አሁን በሃገራችን ያለው ችግር በፖለቲካ ድርጅቶች እና በፖለቲከኞች ብቻ የሚፈታ ችግር እንዳልሆነ በመገንዘብ እንደዚሁም ህዝብ በሙሉ ለለውጡ በሚደረገው ትግል ተሳታፊ ለመሆን መደራጀት እና እራሱን ማዘጋጀት ይኖርበታል።ይህም ሲባል ከሚደርስብን ችግር እና ሰቆቃ ለመላቀቅ ሲባል አስፈላጊውን መስዋእትነት ለመክፈል እራሳችንን ማዘጋጀት ይኖርብናል።

በመሆኑም **የአገዛዙን የሃገር እና የህዝብ ጠላትነት በመረዳት ይህ ስርአት በሃገራችን በቆየ ቁጥር የሚመጣውን መዘዝ እና ስቃይ በማሰብ ሃገር አድኑን ትግል እናግዝ እንቀላቀል? ይህ ካልሆነ በቀር ህዝባችን መሰደዱም በተሰደደበት ቦታ ሁሉም መዋረዱ መሰቃየቱም አይቀርም።**

ህዝብ አሸናፊ ነው!!!